

## በምርመራው ወቅት

# ጥገኝነት የመጠየቅ

→ አገርዎ ለእርስዎ ደህንነቱ የተጠበቀ ስላልሆነ መመለስ ካልቻሉ፣ **እዚህ ጥገኝነት መጠየቅ ይችላሉ።**

→ ያለ ፓስፖርት ወይም ቪዛ ከመጡ፣ **በ4 የምርመራ ፍተሻዎች** ውስጥ ማለፍ አለብዎት።

**ከ18 ዓመት በታች እና ብቻዎን ከሆኑ፣ ለፖሊስ መኮንኖች ወዲያውኑ ይንገሩ።**

እርስዎን ለመደገፍ ተንከባካቢ የሚባል ሰው ይመድቡልዎታል።

## የማንነት እና የደህንነት ፍተሻዎች

- የፖሊስ መኮንን ወይም የድንበር ጠባቂ **ስምዎን፣ ዕድሜዎን፣ የመጡበትን ቦታ እና የጉዞ ዝርዝሮችን** ይጠይቃሉ።
- ከ6 ዓመት በላይ ከሆነ ሰው ሁሉ **ፎቶ እና የጣት አሻራ ይወስዳሉ።**
- ምርመራው እስኪያልፍ ድረስ **ሊፈተሹና** ንብረቶችዎ ሊወሰድብዎት ይችላሉ።
- እንደ መታወቂያ ካርድ ወይም የልደት የምስክር ወረቀት ያሉ ሰነዶችዎን በሙሉ፣ በስልክዎ ላይ ያሉ ፎቶዎች ቢሆኑም እንኳ፣ **ለመኮንኖቹ ያሳዩ።**

## የጤና እና የተጋላጭነት ፍተሻዎች

- **ሐኪም ወይም ነርስ** ለበሽታዎች እና ለሌሎች የጤና ችግሮች ይፈትሹዎታል።
- **የህክምና ሪፖርቶችዎን** ወይም የክትባት ካርድዎን ካለዎት ያካፍሉ።
- **የሰለጠኑ ሰራተኞች ይረዱዎታል።** የተጨነቁ፣ ያዘኑ፣ የፈሩ እንደሆነ ከተሰማዎት ወይም የቤተሰብ አባላትዎን የሚፈልጉ ከሆነ ይንገሯቸው።
- **የሚያጋሩት ነገር ሁሉ ምስጢራዊ ሆኖ የሚቆይ ሲሆን** ከትውልድ አገርዎ ባለሥልጣናት ጋር አይጋራም።

ፍተሻዎቹ እስከ **7 ቀናት** ሊወስዱ ይችላሉ።
በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ምርመራው በሚካሄድበት ቦታ ይቆያሉ።

## ያስታውሱ

- ለጥገኝነት ከጠየቁ፣ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት በተቻለ ፍጥነት እርስዎን መመዝገብ አለባቸው።
- ምክር ለማግኘት ጠበቃ ይጠይቁ እና ቋንቋውን ካልተረዱ አስተርጓሚ ይጠይቁ። ድጋፋቸውን ከክፍያ ነጻ ያገኛሉ።
- እዚህ የሚሠሩ ሁሉም ሰዎች በአክብሮት ሊይዙዎት ይገባል።
- ከመኮንኖቹ ጋር ይተባበሩ እና የሚሉት ነገር ግልጽ ካልሆነ ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲያስረዱዎት ይጠይቋቸው።
- መመለስ ከፈለጉ፣ አማራጮችዎን ለማወቅ መኮንኖቹን እርዳታ ይጠይቁ።



Amharic

euaa EUROPEAN UNION AGENCY FOR ASYLUM

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025